በ 29. አፕሪል 2020 ዓ.ም.

**የሄሰን፡ ማህበራዊ፡ ጉዳይና፡ ውሕደት፡ ሚኒስቴር፡ የኮሮና፡ ቫይረስን፡ በተመለከተ፡ ማስረጃ፡፡**

ቀጥሎም፡የኮሮና፡ቫይረስን፡ በተመለከተ፡አንዳንድ፡ወቅታዊ፡መረጃዎችንና፡
የጥቆማ፡ምንጮችን፡የት፡ማግኘት፡እንደሚችሉ፡እንነግርዎታለን ፡፡

በ 20019 ዓ.ም. መጨረሻ፡ላይ፡የዓለም፡ጤና፡ድርጅት፡ WHO በ ዉሃን [ ቻይና ] መንስሄው፡ ባልታወቀ፡ ምክንያት፡ በርካታ፡የሳምባ፡መታመም፡እንደተከሰተ፡ገልጿል፡፡ ከ ጥቂት፡ቀናትም፡በኋላ፡ መንስሄው፡አዲስ፡ዓይነት፡ቫይረስ፡እንደሆነ፡ለማወቅ፡ተችሏል፡፡ SARS-CoV- 2 ይባላል፡፡ በዚህ፡ቫይረስ፡ምክንያት፡የተፈጠረው፡በሽታ፡ COVID-19 ሲባል፡ባሁኑ፡ ወቅት፡በመላው፡ዓለም፡ላይ፡እየተሰራጨ፡ይገኛል፡፡

<u>**በሚከተሉት፡ገጾች፡ውስጥ፡**</u>

1. ስለ፡ኮሮና፡ቫይረስ፡አጠቃላይ፡ መረጃዎች፡
2. ጤንነቴን፡ጠብቄ፡ለመቆየት፡እኔ፡ራሴ፡ምን፡ዓይነት፡ቅድመ፡ጥንቃቄ፡ማረግ፡እችላለው ?
   ምልክቶቹ፡ቢታዩብኝ፡ማረግ፡ያለብኝ፡ምንድነው ?
3. በሄሰን፡ ስላለው፡የጭምበል፡ማረግ፡ግድጅን፡ በተመለከተ፡መረጃዎች፡፡
4. በሄሰን፡ ስላለው፡ የርቀት፡መስፍረት፡ትእዛዝ፡ በተመለከተ፡መረጃዎች፡፡
5. ከጉዞዎቻቸው፡ለሚመለሱና፡ወደ፡ሄሰን፡ለሚገቡ፡ሰዎች፡መረጃዎች፡፡
6. በሄሰን፡ ስለ፡ጸሎት፡ቤት/ቅ ዳሴ/ ፥ የቀብር፡ስነስራትን፡በተመለከተ፡መረጃዎች፡፡
7. በሄሰን፡ ስለ፡ወሊድ ፡ጊዜ፡እንዲሁም፡በሞት ፡ሂደት፡ወቅት፡ቤትሰብ፡አብሮ፡ማጀብን፡በተመልከተ፡መረጃዎች፡፡
8. በሄሰን፡ ሕጻናትን፡መንከባከብ፡ረገድ፡ መረጃዎች፡፡

## 1. አጠቃላይ ፡ መረጃዎች ፡

### ወቅታዊው፡ሁኔታ፡ምን፡ይመስላል ?

የሮበርት፡ኮህ፡ኢንስቲቱት፡ ( R K I ) በ የጊዜው፡ ይህ፡ አዲሱ፡ ቫይረስ፡ በጀርመን፡ አገር፡ ለሕብረተሰቡ፡ ጤና፡ ምን፡ ማለት፡ እንደሆነ፡ ይገመግማል፡፡ የወቅታዊ፡ አደጋ /ሥጋትን ፡በተመለከተ፡ **R K I** በሚቀጥለው፡ አድራሻ ፡ይፋ፡ ያረጋል፡፡

https://www.rki.de/DE/Content/InfAZ/N/Neuartiges_Coronavirus/Risikobewertung.html;jsessionid=9766CE9E961256ECB36D5D17A325E8F4.internet062.

ለሄሰን፡የሄሰን፡አገር፡መንግስት፡የወሰነው ፥ የኮሮና ፡ቫይረስ ፡መስፋፋትን፡ ቢያንስ፡ለመቀነስ፡ እና፡ ሰዎችን፡ አደጋ፡ ላይ፡ ላለመጣል፡ ሲባል፡ የግል ፡ግንኙነቶችን፡ ማለትም - በህብረተሰቡ ፡ውስጥም፡ሆነ ፡በግል፡ ስፍራዎትም - በተቻለ፡ መጠን፡ ግኑኝነት፡ መቀነስ ፡ያስፈልጋል ፡፡ ስለ ፡ጭምብል፡ ግዳጅ፡ እና ፡የርቀት፡መስፍረትን፡በተመለከት፡ በሚቀጥሉት፡ ገጾች ፡ላይ፡ተጨማሪ፡ መረጃ ፡ማግኘት ፡ይቻላሉ ፡፡

### በሄሰን፡ውስጥ፡ አጠቃላይ፡የኮሮና፡ቫይረስን፡በተመለከተ፡ሌላ፡መረጃዎች፡የት፡ማግኘት፡እችላለው ?

ወቅታዊ፡ መረጃዎችን፡ በ ሄሰን፡ የ ማሕበራዊና፡ውሕደት፡ምኒስቴር፡ ገጽ፡ በ ሚከተለው ፡ሊንክ፡ገብተው፡ ያገኛሉ፡፡ www.hessenlink.de/2019ncov.

የሄሰን ፡የማህበራዊና፡ውሕደት፡ሚኒስቴር፡ እንዲሁም፡ የሄሰን፡አገር፡ ከከፍያ፡ ነጻ፡የሆነ፡ የመረጃዎች፡ማግኛ፡የስልክ፡ቋሚ፡መስመር፡ ለ ሴቶችና፡ወንዶች፡ ዜጎች ፡ አዘጋጅተዋል፡፡

- **የኮሮና ቫይረስን፡ አስመልክቶ፡ ስለ፡ሕክምና፡ወይም፡ የጤና፡ነክ፡ጥየቂዎች፡**

  የኮሮና፡ስልክ፡መስመር፡ 0800 555 4 666

  መገኛ፡ሰዓት፡ በየቀኑ፡ከ 8 እስከ 20 ሰዓት፡፡

ማንኛውም ፡ዜጋ፡ጥያቄ ካለው፡ ተጠያቂውን፡የጤና ፡ክፍል፡ ማነጋገር፡ ይችላሉ ፡፡ አድራሻዎች፡ከዚህ፡ያገኛሉ፡፡ https://tools.rki.de/PLZTool/.

## 2. በጤንነት፡ለመቆየት ራሴ፡ምን፡ዓይነት፡ቅድመ፡ጥንቃቄ፡ማድረግ፡እችላለሁ ?

የመከላከያ፡ እርምጃ፡ይሆን፡ዘንድ፡ / ጉንፋንንም፡ጨምሮ / ዜጎች፡በሙሉ፡ የሚከተሉ ትን፡ ሕግጋት፡ እንዲያከብሩ፡በጥብቅ፡ይጠየቃሉ፡፡

- ብዙ፡ጊዜ፡ እና፡በደንብ፡እጅዎትን፡መታጠብ፡፡ ( ሕጻናትም፡ሆኑ፡ወጣቶችም፡ጭምር )
- መሳልና፡ማስነጠስ፡በ ወረቀት፡መሃረብ፡አልያም፡በክንን፡ አካባቢ፡ብቻ፡፡ (ሕጻናትም፡ሆኑ ወጠቶችም፡ጭምር )
- መሃረብዎትን፡አንድ፡ጊዜ፡ብቻ፡ይጠቀሙ፡ከዛም፡በየጊዜው፡ከተጠቀሙበት፡በኋላ፡ወደ፡ቆሻሻ፡ መጣያ፡ውስጥ፡ይጨምሩ፡፡
- እጅ፡መጨበጥ ፥መቃቀፍ ፥ መሳሳም፡ አይቻልም፡፡
- በእጅዎት፡አፍንጫዎትን ፥አፍዎትን ፥እንዲሁም፡ዓይንዎትን፡እንዳይነካኩ፡፡ (በብዙ፡ሰዎች፡ ሊያዙ፡የሚችሉ፡እንደ፡አቶቢስ፡ውስጥ፡መደገፊያ፡ወይም፡የበሮች፡መክፈቻዎች፡፡እራስዎ፡ ቤት፡ውስጥም፡ቢሆን) ፡፡
- ስማርት፡ፎን ፥ሞባይል ፥ታብሌት ፡ ወዘተ የመሳሰሉትን፡በየጊዜው ፡በ ጸረ፡ተባይ፡ማጥፊያ፡ ማጽዳት፡፡
- ከመሰረቱ፡ጀምሮ፡የራስዎትን፡ ብርጭቆንቅና፡ ቁሳቁስ፡ይጠቀሙ፡፡
- ሰዎች ፡የተሰበሰቡበት፡ቦታ፡ በጭራሽ ፡እንዳይገኙ፡፡

### ምልክቶቹ፡ሲታዩብኝ፡ማረግ፡ያለብኝ፡ምንደነው ?

ዜጎች፡የ ሕመሙ፡ ምልክቶች፡ማለት፡እንደ፡ሳል ፥ትኩሳት ፥ወይም ፡ የመተንፈስ ፡ ችግር፡ካለብዎት ፥

- **116 -117 anrufen** ይደውሉ ፡ ( የተረኛ፡ሓኪም፡ስልክ፡ቁጥር )
- ለሚመለከተው፡የአካባቢው፡ የመንግስት፡የጤና፡አካል፡ በስልክ፡ያሳውቁ፡፡
- ለቤት፡ሕኪምዎት፡በስልክ፡ያሳውቁ፡፡

እነሱም፡ ጠያቂው፡ሰው፡ በአዲሱ የኮሮና፡ቫይረስ፡ ኢንፌክሽን፡ መያዝ፡አለመያዙን፡ካጣሩ፡በኋላ፡ በቂ፡የሆነ፡ጥርጣሬ፡ካገኙ፡ለተጨማሪ፡ምርመራና፡ ሕክምና፡የስተላልፋሉ፡፡

በሌላ፡ቋንቋ፡ ተጨማሪ፡ማስረጃ፡ከፈለጉ፡በሚከተለው፡አድራሻ፡ ያገኛሉ፡፡

https://www.bundesgesundheitsministerium.de/coronavirus.html
በአሁኑ፡ወቅት፡በተለያዩ፡የ ሶሻል፡ማስ፡ሚዲያ፡ላይ፡ብዙ፡የተሳሳቱ፡መርጃዎች፡እየተሰራጩ፡ነው፡፡ እባክዎትን፡ ለመረጃዎት፡ከላይ፡የተጠቀሱትን፡ምንጮች፡ይጠቀሙ፡፡

## 3. በሄሰኝ የጨምበል፡ግዳጅን፡በተመለከተ፡መረጃዎች ፡፡

በሄሰን፡ከ 27 አፕሪል 2020 ዓመተ፡ምኅረት፡ጀምሮ፡ በሕዝብ፡ማመላለሻ፡መኪናዎች ፥ ወይም፡በገበያ፡አዳራሾች የሳምንት፡ገበያዎች ፥ባንኮች ፣ፖስታ፡ቤቶች ፥ ወዘተ፡ የሚጠቀሙ፡ዜጎች፡በሙሉ፡የአፍና፡አፍንጫ፡መከላከያ፡ጭምብል፡ማረግ፡አለባቸው፡፡ ይህም፡ከ ስድስት፡ዓመት፡ጀምሮ፡በላይ፡ላለ፡ሰው፡በሙሉ፡ነው፡፡

**የፍና፡አፍንጫ፡ጨምበል፡ማለት፡ምን፡ማለት፡ነው ?**

ማንኛውም፡ የአፍና፡አፍንጫ፡መከላከያ፡ የምራቅ፡ ወይም፡ በሳል፡ወቅት፥በማስነጠስ ፡ወቅት፡ወይም፡ በንግግር፡ወቅት፡አስተላላፊ፡ቅንጣት፡ጠብታዎች፡እንዳይተላለፉ፡የሚከላከል፡ ሁሉ፡እንደ፡አፍና፡አፍንጫ፡የሕክምናደረጃው፡ አይደለም፡፡

ከእራስ፡ሰራሽ ፡ጭምበል፡ሌላ፡እንደ፡ስካርቭ፡ ወይም፡ነጠላ፡ ጠቃሚ፡ናቸው፡፡

የሕክምና፡ባለሙያዎች፡ጭምበል፡ለ ሕክምና፡ባልሙያዎች፡መቀመጥ፡አለበት፡፡

**ርቀትዎን፡መጠበቅ፡ ወደፊትም፡አስፈላጊ፡ነው፡፡**

የግኑኝነት፡ገደቦች፡እና ፡ የርቀት፡ ደንቦች፡ የዕለት፡ተለት፡ጭምብሎች፡ በማረግ፡ የተነሳ፡ አይሻርም፡፡

**ልዩ፡ሁኔታዎች፡**

ይህ፡ የአፍ / አፍንጫ፡መከላከያ፡ጭንብል፡ ግዳጅ፡ ከ 6 ዓመት፡በታች፡የሆኑ፡ሕጻናትን፡ወይም፡ በጤናቸው፡ላይ፡ችግር፡ያለባቸውን፡ሰዎች፡ወይም፡ለአካለ፡ስንኩል፡ሰዎች፡አይመለከታቸውም፡፡

**የገንዘብ፡ቅጣት፡፡**

ጭንብል፡አለማረግ ፡ስነስራት፡እንደ፡ማጉደል፡ይቆጠራል፡፡ ዜጎች፡ጭንብል፡ካላረጉ፡እና፡ ከተነገራቸው፡በኋላም፡ ካላረጉ፡ በድጋሚ፡ትእዛዙን፡በመጣስ፡ምክንያት፡የተነሳ፡እስከ፡50 አይሮ ድረስ የገንዘብ፡ቅጣት፡ሊቀጡ፡ይችላሉ፡፡

## 4. ስለ፡ርቀት፡መስፈር፡ መረጃዎች፡፡

በሕዝብ፡መሰብሰቢያ፡ክፍሎች፡ ወይም፡ አደባባይ፡ ላይ፡መገኘት፡፡የሚቻለው፡ ለብቻዎት፡አልያም፡

አብርዎት፡እቤትዎ ፡ከሚኖሩ፡ዘመዶች፡ጋራ፡ ወይም፡ከ **አንድ፡ አብርዎት፡እቤት፡ውስጥ ፡ከማይኖር፡**

ሰው፡ጋራ፡ ብቻ፡ነው፡፡

ለየት፡ካሉ፡ሁኔታዎች፡ በስተቀር፡፡

- የሕዝብ፡ማመላለሻ፡፡
- ከዓቅመ፡ዓዳም፡ በታች፡ለሆኑ፡ልጆችና፡እርዳታ፡ለሚያስፈልጋቸው፡
- ሰዎች፡፡ፈተናዎች፡ለመፈተን፥በተለይ፡የመንግስት፡ፈተናዎችና፡የሙያሂደት፡ፈተናዎች፡፡ድ
- ደም፡ለመለገስ፡፡
- በንግድ፡ሥራ፥ በሙያ፡ሥራ፥ ለአገልግሎት፡ሥራ ፥ወይም፡ በእንክብካቤ፡ጉዳይ፡ረገድ፡ተገናኝተው፡ ለሚሰሩ፡ሰዎች፡፡
- ለስብሰባና፡ለፍርድ፡ቤት፡ድርድር፡፡
- አስፈላጊ፡ከሆነና፡ከመንግስት፡አካል፡ፈቃድ፡ከተሰጠ፡ለ ህዘን ፡ጊዜ፡ እንዲሁም፡ለቀብር፡ጊዜ፡፡ከ ጉዞ

አስፈላጊ፡ከሆነና፡ከመንግስት፡አካል፡ፈቃድ፡ከተሰጠ፡ለ ህዘን ፡ጊዜ፡ እንዲሁም፡ለቀብር፡ጊዜ፡፡ከ ጉዞ

## 5. ከጉዞ፡ለሚመለሱና፡ወደ፡አገር፡ለሚገቡ፡፡

**ከጉዞ፡ተመላሾችና፡ወደ፡አገር፡ለሚገቡ ፣ ለምሳሌ፡ከ እረፍት፡ለሚመልሱ፡ ምን፡መጠንቀቅ፡አለባቸው?**

ወደ፡አገር፡በሚገቡና፡ከእረፍት፡የሚመለሱ፡ሰዎች፡ምክንያት፡ሌለ፡አዲስ፡የኢንፌክሽን፡ማእበል፡ እንዳይሰራጭ፡ከ 10 አፕሪል፡2020 ዓ.ም. ጀምሮ፡ ወደ፡አገር፡ለሚገቡ፡ሰዎች፡ ተለይተው፡የ 14 ቀን፡ የቤት፡ውስጥ፡ቆይታ፡እንዲያረጉ፡ተወስኗል፡፡

ይህ፡ትእዛዝ፡ በተጭማሪ፡ የሚያክለው፡ከ ውጭ፡አገር፡ቆይታ፡በኋላ፡ወደ፡ሄሰን፡የሚገቡ፡ ወዲያውኑ፡ በሚኖሩበት፡አካባቢ፡ላለው፡የመንግስት፡የጤና፡ አካል፡ኮንታክት፡ማድረግና፡ስለ፡መመለሳቸውም፡ማሳወቅ፡ግዴታ፡አለባቸው፡፡

ከዚህ፡በተረፈ፡ የ ሮበርት፡ኮህ፡ኢንስቲቱት፡ባወጣው፡የኮቪድ፡19 በሽታ፡መመዘኛ፡መሰረት፡ምልክቱ፡ከታዩብዎት፡ወዲያውኑ፡ለሚመለከተው፡የመንግስት፡ጤና፡አካል፡ማሳወቅ፡አለብዎት፡፡

ለተወሰኑ፡ሰዎችና፡ለተወሰኑ፡ሙያዎች፡ ልዩነት፡ይደረጋል፡፡ በተለይ፡ ሕቡን፡በቁሳቁስ፡በማቅረብ፡ለሚያገለግሉ፥የሕዝብ፡ማመላለሻ፡ትራንስፖርት፡ወይም፡በጤና፡ነክ፡ነገሮች፡መስክ፡ አስፈላጊ፡ከሆነና፡

በተጨማሪ፡ የአደጋ፡ጊዜ፡ረዳት፡አገልጋዮች፡ለምሳሌ፡እንደ፡ፖሊሶች፡፡ ከዚህም፡ውጪ፡ሌላ፡ አብረው፡ያልተጠቃለሉት፡ ትራንዚት፡ወይም፡ጥቂት ቀን፡በሄሰን፡ አልያም፡በውጭ፡አገር፡ቆይታ፡ለሚያረጉ፡፡

## 6. ስለ፡ጸሎት፡/ ቃዳሴ፡እንዲሁም፡የሓዘን፡/ለቅሶ፡ስነስራት፡መረጃዎች፡፡

<u>የርቀት፡</u> መስፈርን፡እንዲሁም፡የንጽሕና፡ደንቦችን፡በደንብ፡ከተከተሉ፡ቅዳሳሴም፡ሆነ፡ የሕይማኖት፡ ስብሰባዎች፡ በድጋሚ፡ሊከናወኑ፡ይችላሉ፡፡ ምንም፡እንኳን፡በተለመደው፡ሁኔታ፡ባይሆንም፡ ሰዎች፡በጋራ፡እምነታቸውን፡እንዲቀጥሉና፡ ቅዱስ፡ቁርባና፡ እንዲፈጽሙ፡መገናኘት፡ይችላሉ፡፡

ከ 4 ማይ፡ጀምሮ፡ቅዳሴም፡ሆነ ፡የሕይማኖት፡ስብሰባ፡ለማረግ፡ይቻላል፡፡

- በሰዎች፡መካከል፡ቢያንስ 1,5 ሜትር ርቀት፡ መኖር፡አለበት፡፡
  (ይህ፡ዝቅተኛ፡የርቀት፡መጠን፡በአንድ፡ቤት፡ውስጥ፡አብረው፡የሚኖሩ፡ሰውች፡አይመለከትም)

- እቃዎች፡ ለምሳሌ የመጽዋት መስጫ፡ሳጥን፡ ተቀብሎ፡ማስተላለፍ፡አይቻልም፡፡
- ብቁ፡የንጽህና ፡እርምጃዎች፡ለምሳሌ፡እንደ፡ ጸረ፡ተባዮች፡ማጥፊያ፡ከተዘጋጀ፡፡
- ከዚህ፡በተረፈ፡ የእምነት፡ማህበረሰቦች፡ ስለ አስፈላጊው፡የርቀት፡መስፈርትንና፡ስለ፡ንጽህና፡ርምጃዎች፡በስብሰባው፡ቦታ፡ላይ፡በደንብ፡የሚታይበት፡ቦት፡መስቀል አለባቸው፡፡

  ከላይ፡የተጠቀሱትን፡ነጥቦች፡በትክክሉ፡ከተጠቀሙ፡የሀዘን፡ጊዜ፡ወይም፡በቀብር፡ሥነስራት፡ወቅት፡መሰባሰብ፡ይቻላል፡፡

## 7. በወ ሊ ድ፡ጊዜ፡ወይም፡ በ ቀ ብ ር፡ስነስራት፡ላይ፡በቤተሰብ፡ስለመታጀብ፡ መረጃ፡፡

- የአዛውንቶች፡ተንከባካቢዎች፡ ከ 28 ማርች 2020 ዓ.ም. ጀምሮ በተናጠል፡ለቅርብ፡የቤተሰብ፡አካል፡ለሆነ፡ ሰው፡ እስካሁን፡ ተፈጻሚነት፡ካለው፡ሕግ፡የተለየ፡ የጉብኝት፡ጊዜ፡ሊፈቀድላቸው፡ይችላል፡፡ የቤቱ፡ሥራ፡አስኪያጅ፡ ለምሳሌ፡ የሆስፒታሉ፡ ስራ፡አስኪያጅ፡ - የሚያክመው፡ሐኪም፡ከ ሥነ፡ምግባርና፡ ማህበራዊ፡ ጉዳይ፡አንጻር፡ የቅርብ፡ቤተሰብ፡የሆነ፡ሰው፡በ ወሊድ ወይም፡በሞት፡ጣር፡ወቅት፡ቢያጅብ፡ተገቢ፡ሆኖ፡ካገኘው፡ ሊፈቅድ፡ይችላል፡፡

የመተንፈሻ፡አካላት፡ኢንፌክሽን፡የለባቸው፡ሰውችን፡ አያካትልም፡፡

ይህ፡ድርጊት፡፡“ የኮሮና፡ ቫይረስን ፡ለመዋጋት፡የወጣ፡ሁለተኛ፡ትእዛዝ “፡ከሚለው፡ ለየት፡ያል ፡ነው፡፡

**8. ሕጻናትን፡ስለመንከባከብ፡መረጃዎች፡፡**

በሄሰን፡ የቫይረሱን፡የመሰራጨት፡ ፍጥነት፡ለመቀነስ፡ችለናል፡፡ ወደፊትም፡ዓላማችን፡ሰውን፡ሁሉ፡ለመከላከል፡ በተለይ፡ አዛውንቶችን፡እና፡በሽተኞችን፡ለመንከባከብ፡ነው፡፡ ስለዚህም፡ አዲስ፡የኢንፌክሽን፡ማእበል፡በተቻለ፡መጠን፡መወገድ፡አለበት፡፡ እዚህም፡ለመድረስ፡ሁነኛው፡እርምጃ፡እንደበፊቱ፡አሁን ም፡የግል፡ግኑኝነት፡መቀነስ፡ነው፡፡ ሌሎቹም፡የቀሩ፡ገደቦች፡፡ሁሉ፡ይህንን፡መህር ይከተላሉ፡፡ ስለዚህ፡እስከ 10.ሜይ 2020 ዓ.ም. ድረስ፡ ልጆች፡ወደ፡ሕጻናት፡መዋያ፡ እና፡ሌሎች፡የ ሕጻናት፡እንክብካቤ፡ማእከላት፡መሄድ፡አይችሉም፡፡ ድንገተኛ፡የሕጻናት፡መንከባከቢያ፡ይቀጥላል እንደ፡አስፈላጊነቱም፡ ኢንፌክሽኑን፡ለመከላከል፡ሲባል፡ግሩፑን፡አነስ፡ማረግ፡አላበለዚያ ፡ እርምጃዎቹ፡ውጤታማ፡አይሆኑም፡፡

**ለምን፡ያህል፡ጊዜ፡ነው፡ልጄ፡ሕጻናት፡መዋያ፡መሄድ፡የማይችለው ?**

ለጊዜው፡እስከ፡10 ሜይ ድረስ፡፡

**የሕጻን ፡ሞግዚቷ፡ለጀን፡መንከባከቧን፡መቀጠል፡ትችላለች ?**

አይሆንም፡ ተዛዙ፡ለ ሕጻናት፡መንከባከቢያ፡ማእከሎችንም፡ያጠቃልላል፡፡ የልጆቹ፡ወላጆች፡ በሕጻናት፡መንከባከቢያ፡ማእከላትና፡ሕጻናት፡መዋያ፡ መግባት፡ከልክልነትን፡ማክበር፡አለባቸው፡፡

**በዚህ፡የማይካተቱ፡አሉ፡ ?**

አዎ፡፡ ለተወሰኑ፡የሙያ፡ክፍሎችና፡ ሰዎች፡ የአደጋ፡ጊዜ ፡የሕጻናት፡መንከባከቢያ፡ማእከሎች፡አሉ፡፡

ለአደጋ፡ጊዜ፡የሕጻናት፡መንከባከቢያ፡ ቦታ፡ለማግኘት፡መመዘኛው፡ የልጁ፡ አንድ፡ሥራ፡የምትሰራ፡የአሳዳጊነት፡መብት፡ያላት፡/ አንድ ፡ሥራ፡የሚሰራ፡የአሳዳጊነት፡መብት፡ያለው/ በሚቀጥሉት፡

1. የፖሊስ፡ምርመራ፡አስፈጻሚ፥የመንግስት፡ ፖሊስ፡መስሪያ፡ቤት፡እና፡ የአስፈስሚነት፡ተግባር፡ፈጻሚ፡ዘመዶች፡፡
2. ለእሳት ፡አደጋ፡መከላከያ፡ቡድን፡[ ቅጥር፡እና በጎአ፡ድራጊ፡ፈቃደኛ፡] የመስሪያ፡ቤቶች፡የእሳት፡አደጋ፡ሰራተኞች ዘመድ፡፡
3. የመንግስት፡የጤና፡አገልግሎት፡አካል፡ሰራተኞች፡፡
4. ዳኞች፤አቃቤሕጎች ፡እና፡የፍትህ፡ጠበቆች፡፡
5. የፍትህ፡ሰራተኞች ፡እና፡ አስከባሪዎች ፡፡
6. የአምቡላንስ፡ሰራተኞች፡
7. የቴክኒክ፡ድጋፍ፡ሰጪ፡መስሪያቤት፡ረዳቶች፡
8. የአደጋ፡ጊዜ፡መከላከያ፡ረዳቶች፡፡
9. 9. በ ጤና፡ተቋሞች፡ ክሊኒኮች፡ሆስፒታሎች፡እና የአዛውንቶች፡መንከባከቢያ፡ተቋማት፡እና፡በ ቤት፡ውስጥ፡ተንከባካቢና፡ነርስ፡እንዲሁም፡የአዝውንቶች፡ተንከባካቢ፡፡
10. በሕክምና፡ሙያ፡ዘርፍ፡ላይ፡በተንከባካቢነት፡፡የተሰማሩ፡በተለይ፡

-- የአዛውንቶች፡ተንከባካቢ፡ረዳቶች፡፡

-- የአነስቴዚ፡ረዳቶች፡፡

-- ሃኪሞች፡

-- ፋርማሲስቶች፡

-- ተህዋስያን፡አጥፊዎች፡

-- የጤና ፡የህጻናት፡ነርሶች ፣እና፡የጤና፡ነርስ፡እንዲሁም፡ተንከባካቢ፡፡

-- አዋላጆች፡፡

-- የነርስ፡ረዳቶች፡

-- የሕክምና፡ባለሙያ፡ሰራተኞች፡፡

-- የሕካምና/ቴክኒክ፡ላቦራቶሪ፡ ፡

-- የሕክምና/ቴክኒካል፡ራዲሎጊ፡ረዳቶች፡፡

-- የሕክምና/ ቴክኒካል፡የተግባራዊ፡ምርመራዎች፡ረዳቶች፡፡

-- የአምቡላንስ፡የአደጋ፡ጊዜ፡ረዳቶች፡

-- የኦፐርሲኦን፡ቴክኒክ፡ረዳቶች፡፡

-- ባ ለሙያ፡ነርሶች ፡፡ሴቶችም/ወንዶችም፡፡

-- የፋርማሲ፡ቴክኒካል ረዳቶች ፡፡

-- የአምቡላንት፡ረዳቶች፡ በ § 1 የአምቡላንስ፡ሕግ፡መሰረት ፡

-- የ የጥርስ፡ሕኪሞች፡፡

-- የጥርስ፡ሕክምና፡ሙያ፡ሰራተኛ፡

-- የ ስነ፡ልቦና፡ሓኪሞች፡እና፡የልጆችና፡ወጣቶች፡፡

11. ለሙዓለ፡ሕጻናት፡ የሙያተኛ፡ሃይል፡በ § 25 HKJGB

11a. በ § 45 SGB VIII መሰረት፡ የስራ ፡ፈቃድ፡ያለው[ በከፊል]፡፡ ቋሚ፡የሕክምና፡ ተቋም ፡፡ለልጆች ፡መዋያ፡ግን፡ያልሆነ፡

11b. በተለይ፡ በስነልቦና፡መስክ፡በአደጋ፡ጊዜ ፡እንክብካቤ፡ሙያ፡ለተሰማሩ ፣ ወይም፡የአደጋ ጊዜ፡ስልክ፡ላይ፡የሚያገለግሉ ፡፡ በጾታ፡ነክ፡ጉዳይ፡ምክንያት፡ለተበደሉ፡በተለይ፡የሴቶች፡ቤት፡ወይም፡የጥገኘንት፡ቤቶች፡ ሰራተኞች፡፡

11c በ እርግዝና፡ጊዜ፡ችግር ሕግ፡መሰረት የሚሰሩ፡እውቅና፡ባላቸው፡የእርግዝና፡ወቅት ፡ችግር፡አማካሪ፡ሰራተኞች፡፡

11d. 11c. እውቅና፡ባለው፡የእርግዝና፡ግጭት፡ማእከላት፡ውስጥ፡በእርግዝና ግጭት ሕግ፡መሰረት ምክክር የሚያደርጉ፡ሰዎች፡፡

በሕዝብ፡ድርጅቶች ውስጥ፡በ ሕጻናታ፡ወጣቶች፡አጠቃላይ፡ማህበረአዊ፡አገልግሎት፡ሰራተኛ፡፡

12. በ SGB II, SGB III, SGB XII, ሕግ፡መሰረት፡በቀጥታ፡ከስደተኛ፡እርዳታ፡ገንዘብ፡ክፍያ፡ጋራ፡በተያያዘ፡የሚሰሩ፡ሰራተኞች፡፡

13. በተወሰኑ፡ወሳኝ፡መስኮች፡ውስጥ፡ በተለየ፡ፈቃድ፡ወረቀት፡ለሚስሩ፡ሰራተኞች፡ለምሳሌ፡ የምግብ፡ችርቻሮ፡ሱቆች፡ሰራተኞች ፣በግብርና፡መስክ፡ እንዲሁም፡በ ማዘጋጀቱም፡ስራ ፣በማጓጓዙ፣ በማከፋፈሉ፡ተግባር፡ላይ፡የተሰማሩ፡ሰራተኞች፡፡

14. በቆሻሻ፡መስብሰብ፡ሙያ ላይ፡ለተሰማሩ፡በተለየ፡ፈቃድ፡ በቦታው፡ላይ መገኘቱ፡አስፈላጊ፡ሆኖ፡ከተገኘ፡፡

15. በ ዋና፡ሙያቸው፡በ ጋዜጠኛነት ፥ በራዲዮ፡ጣቢያ፥በቴለቪዥን፡ጣቢያ፥ እና፡በ
ሌላም፡የዜና፡ማሰራጫ፡ወስት፡ለሚሰሩና፡በስራ፡ቦታ፡ላይ፡መገኘታቸው፡አስፈላጊ፡ሆኖ፡ከተገኘ፡፡

16. ወታደሮች፡እንዲሁም፡በ የጦሩ፡ስራ፡ባልደረቦች፡ለደህነቱ፡ጥበቃ፡በቦታው፡ላይ፡አስፈላጊ፡ሆነው፡ከተገኙ፡፡

17. የ ት/ም ቤት፡ሃላፊዎች፣አስተማሪዎችና፡ረዳት፡ሃይሎች፡ በቀጥታ፡ከበቅንብሩና፡ ት/ም አሰጣጥ፡ላይና

ሌሎች፡የት/ም ነክ፡ነገሮች፡ላይ፡አስፈላጊ፡ከሆኑ፡፡

18. ለብቻ፡አሳዳጊ፡ሙያተኛ፡ሰራተኛ፡[ ለአንድ፡ወይም፡በርካታ፡ከአቅመ፡አዳም ያነሱ፡ልጆች፡አሳዳጊ]

በ
ሕጻናት፡መዋያ፡ውስጥ፡የሚሰሩ፡ሰራተኞች፡የኢንፌክሽን፡መከላከያ፡ደንቡን፡ከተከተሉ፡፡በሚሰሩበት፡ቦታ፡የራሳቸውን፡ልጆች፡ይዘው፡
መምጣት፡ይችላሉ፡፡ በወጣቶች፡እንክብካቤ፡ማእከላት፡
በኩል፡ለተወሰኑ፡ልጆች፡የመዋለ፡ሕጻናት፡ወይም፡የሕጻን፡መንከባከቢያ፡ቦታ፡አስፈላጊ፡መሆኑ፡ከተረጋገጠ፡እገዳው፡
እነሱን፡አያካልልም፡፡ከላይ፡የተጠቀሱትን፡ነጥቦች፡ማሟላት፡አለማሟላታቸውን፡ተቋሙ፡ማስረጃ፡ሊጠይቅ፡ይችላል፡፡